


# የኢትዮጵያ ሴት ልጆች ማኒፌስቶ

2017

MALALA FUND SUPPORTER

EDUCATION CHAMPION NETWORK ETHIOPIA

NEWA



# የኢትዮጵያ ሴት ልጆች ማኒፌስቶ
2017

MALALA FUND SUPPORTER

EDUCATION CHAMPION NETWORK ETHIOPIA

NEWA

# ማውጫ


| | |
|---|---|
| መግቢያ | 4 |
| መቅድም | 5 |
| ለተግባራዊ የለውጥ እርምጃ የተደረገ ጥሪ | 7 |
| ድምጻችን ይሰማ፤ ውክልናችን ይረጋገጥ | 12 |
| ባለድርሻ አካላት ንቅናቄያችንን እንዲቀላቀሉ ጥሪ እናቀርባለን | 18 |



# መግቢያ

እኛ ከተለያዩ የሀገሪቷ ክልሎች የተውጣጣን ኢትዮጵያውያን ሴት ልጆች የጋራ በሆነ ቁርጠኛ መንፈስ፤ አጠቃላይ መብቶቻችንን እና የትምህርት ዕድል የማግኘት መብታችንን ለማስከበር ተሰባስበናል። በኢትዮጵያ ሴቶች ማህበራት ቅንጅት ማዕቀፍ እና በማላላ ፈንድ ድጋፍ፤ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ-መንግሥት እና በአለም አቀፍ ስምምነቶች የተደነገጉ የሰብአዊ መብቶችና የሴቶች መብቶች ላይ ያተኮሩ ስልጠናዎችን ወስደናል። በየክልላችን በቤተሰብ፣ በማህበረሰብ እና በማህበረሰብ ደረጃ ያለንበትን ደረጃ ለመፈተሽ የባለሙያዎችን ምክር በመውሰድ ስለ ጉዳዩ ጥልቅ ግንዛቤን አግኝተናል። የጋራ አጀንዳዎቻችንን ተወያይተናል፣ ለይተናል፣ በህብረተሰቡ ውስጥ ያለንበትን ደረጃ ለማገናዘብ፣ ስጋቶቻችንን ለመጋራት እና በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እና ህጋዊ ጉዳዮች ላይ ጥያቄዎቻችንን እና ቅድሚያ የሚሰጧቸውን ጉዳዮችን ለመግለጽ ተሰብስበናል። በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የተካሄዱ ክልላዊ ምክክሮችን ተከትሎ፣ የግል ተሞክሮዎቻችን እንዲሁም ጥያቄዎቻችን ይህንን የሴት ልጆች ማኒፌስቶ ለማዘጋጀት ረድቶናል።

ይህ ማኒፌስቶ የእኛን ራዕይ እና ምኞቶች ይይዛል። አጠቃላይ ጉዟችንን ለመገምገም እና ወሳኝ ግብአቶችን ለማግኘት በአዲስ አበባ ሀገራዊ የማረጋገጫ አውደ ጥናት አካሂደን በሰፊው ከተወያይን በኋላ አጀንዳዎቻችንን ገምግመን በማረጋገጥ ይህን የኢትዮጵያ ሴቶች ልጆች ማኒፌስቶን ቀርጽን፣ ድምጻችን እንዲሆን አጽድቀነዋል። ይህ የጋራ ድምጻችን በብሄራዊ መድረክ ላይ እኛን የሚወክል ይሆናል።

# መቅድም

ይህ የኢትዮጵያ ሴቶች ልጆች ማኒፌስቶ በቀጥታ ስለራሳችን እና በራሳችን የምንናገርበት የጋራ ድምፃችን ነው። ይህ ማኒፌስቶ ከተለያዩ ክልሎች፣ የኅብረተሰብ ክፍሎች፣ ብሔረሰቦችና የሃይማኖት ቡድኖች በተውጣጣን የኢትዮጵያ ሴት ልጆች የተቀረጸ ነው። እኛ የገጠር እና የከተማ ሴት ልጆች ነን። ከአርሶ አደርና አርብቶ አደር ማህበረሰብ፣ ከአካል ጉዳተኞች፣ እንዲሁም ከመጠለያ ካምፖች የመጣን ሴት ልጆች ነን። ይህ ማኒፌስቶ ልናያቸውና ልንደርስባቸው የምንፈልጋቸው ጥበቃና ከለላ የማግኘት መብታችንን፣ ድምጻችን የሚሰማበትን እንዲሁም ሰብዓዊ መብቶቻችን የሚጠበቁበት ግቦቻችን እና የውትወታ ስልቶቻችን ተለይተው የሚያብራሩበት ሰነድ ነው። ይህም በተገቢው ጊዜ የኛን ውክልና ለማረጋገጥ፣ በሚያሳስቡንና በሚመለከቱን ጉዳዮች ላይ በቂ ውክልና ተሳትፎ እንዲኖረን፤ እንዲሁም ማንነታችን እና በማህበረሰቡ ውስጥ ያለንን ቦታ ለማሻሻልና ለማጎልበት ያግዘናል።

ይህ ማኒፌስቶ የኢትዮጵያ ሴት ልጆች የሚያጋጥሙንን ተግዳሮቶች ለመፍታት የትምህርት፣ የስነተዋልዶ ጤና፣ የሰላምና ደህንነት፣ ደህንነቱ የተጠበቀ የትምህርት አካባቢ፣ እንዲሁም ውክልና እና ተሳትፎን በተመለከተ ያሉንን መብቶች እና ግዴታዎች ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ማዕቀፎችን ይይዛል፤ ያሳያል። ይህ ሰነድ ተሞክሮዎቻችንን፣ ፍላጎቶቻችንን እና ጥያቄዎቻችንን ለማቅረብ ለውትወታ፣ ለምንፈልገው ማህበራዊ ለውጥና ንቅናቄ ጠንካራ መመሪያ ሆኖ ያገለግለናል። ለባለድርሻ አካላት እና ውሳኔ ሰጪዎች በፖሊሲዎች፣ ህጎች፣ በጀት እንዲሁም ትግበራ ላይ ተገቢ የሆነ አሰራር እና ምላሽ አሰጣጥ እንዲኖር ያደርጋል።

ይህ ማኒፌስቶ መብቶቻችንን ለማስከበርና ለሁሉም የኢትዮጵያ ሴት ልጆችና ሴቶች የተሻለች የወደፊት ኢትዮጲያን ለመፍጠር የምናደርገውን የጋራ ጥረት ለመምራት ያለመ ነው።

MALALA FUND SUPPORTER

EDUCATION CHAMPION NETWORK ETHIOPIA

NEWA

# ለተግባራዊ የለውጥ እርምጃ የተደረገ ጥሪ









**የኢትዮጵያ ሴት ልጆች ማኒፌስቶ** 2017



1

## 1.ፍላጎቶቻችን በሀገር አቀፍ የልማት፣ የዲሞክራሲ እና የመልካም አስተዳደር ዕቅዶች ውስጥ እንዲካተቱ ድምጻችን ይሰማ!

እኛ የኢትዮጵያ ሴት ልጆች ድምፃችንና ጥያቄዎቻችን መደመጥና መጉላት አለባቸው ብለን እናምናለን። ይህም  የኛን አመለካከትና ፍላጎቶቻችንን በሁሉም ሕዝባዊ መድረኮች፣ ውይይቶችና በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ ቅድሚያ እንዲሰጠው ያደርጋል።

ይህም ሲሆን በተለይም አድልዎአዊ ማህበራዊ ልማዶች የሚያደርሱት በጎ ያልሆነ ተጽዕኖ፣ በአሁን ሰዓት ያሉትን ግጭቶችና ቀውሶች፣ በነባር የሕግና የፖሊሲ ማዕቀፎች እንዲሁም በሕገ-መንግስታዊ መብቶቻችንን አፈጻጸም፤ በአጠቃላይ የትምህርት ተደራሽነት ላይ ያላቸውን ተጽዕኖ ማጥናትና ግምት ውስጥ ማስገባት በጣም አስፈላጊ ነው።  በእነዚህ ቀውሶች ምክንያት ትምህርት ቤቶች ለረጅም ጊዜ ተዘግተዋል። የማህበራዊ ግንኙነቶች ተዳክመዋል። እነዚህም ችግሮች በአብዛኛው በሴት ልጆች ላይ ተጽዕኖ አሳድረዋል። በመሆኑም ያለእድሜ ጋብቻ፣ የአፍላ ወጣቶች እርግዝና፣ የሕፃናት ጉልበትና ወሲባዊ ብዝበዛ የመሳሰሉ አሉታዊ ውጤቶች የሚያስከትሉባቸውን አደጋዎች ከፍ አድርጓቸዋል።

ስለሆነም እኛ ሴት ልጆች የፖሊሲና የውሳኔ ሰጪ አካላትን በብሔራዊ የልማት፣ የዲሞክራሲ እና የመልካም አስተዳደር ሂደቶች ውስጥ ተሳታፊና ተጠቃሚ መሆናችንን እንዲያረጋግጡ እንጠይቃለን።

2

## 1.የሴት ተማሪዎች ትምህርት ተግዳሮቶች እንዲወገዱ፤ ትምህርት ቤቶቻችንን መልሶ የመገንባት ስራ እና ትምህርታችንን ለማስቀጠል ቅድሚያ እንዲሰጥ እንጠይቃለን!





እኛ ኢትዮጵያውያን ሴት ልጆች ትምህርት ለማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገታችን ወሳኝ የሆነ መሠረታዊ መብት መሆኑን እንገነዘባለን። ይሁን እንጂ ጥራት ያለው ትምህርት እንዳናገኝ በተለይ የባህል ተፅዕኖች እና ከገንዘብ ጋር የተያያዙ መሰናክሎች አሉብን። እነዚህን ተግዳሮቶች ለመቅረፍ ለሁሉም ኢትዮጵያን ሴት ልጆች የትምህርት ዕድሎችን ለማሳደግ የሚያስችሉ ተግባራዊ እርምጃዎችን እናቀርባለን።

# ለተግባራዊ የለውጥ እርምጃ የተደረገ ጥሪ

ሁሉም ልጆች፣ በተለይም ሴት ልጆች ከገንዘብ ጋር ከተያያዙ ጫናዎች ነጻ የሆነ የትምህርት ዕድል እንዲያገኙ የሚያስችሉ ፖሊሲዎችን እንዲያጠናክር፤ የነፃ ትምህርት ዕድል ቀጣይነት እና ቁርጠኝነት እንዲኖር ለመንግስት ጥሪ እናቀርባለን።

በገጠር አካባቢ ትምህርት ቤቶችን በመገንባት፣ የፈረሱትን መልሶ በመገንባትና በመጠገን፣ ሁሉም ሴት ልጆች እኩል የትምህርት አገልግሎት እንዲያገኙና የተሻለ ኢኮኖሚ ድጋፍ እንዲኖራቸው ለማድረግ የበለጠ መዋዕለ ነዋይ ማፍሰስ አስፈላጊ መሆኑን እናሰምርበታለን።

ደህንነቱ የተጠበቀ የትምህርት አከባቢ እንዲኖር፤ እንዲሁም ንጽህናቸው በአግባቡ የተጠበቁ የመጸዳጃ ቤቶች እና ሴት ልጆችን ከጾታዊ ትንኮሳ እና ጥቃት መከላከል የሚያስችሉ እንዲሆኑ ትኩረት እንዲሰጥ እንጠይቃለን።

የንፅህና መጠበቂያ ፓዶች በወር አበባ ወቅት ጤንነታችንን ለመጠበቅ የሚረዱ አስፈላጊ አቅርቦቶች ናቸው። በትምህርት ቤቶች ውስጥ የንፅህና መጠበቂያዎችን ለማቅረብ በመንግስት የተደረጉ ጥረቶችን እናደንቃለን። ምንም እንኳን ይህ ትልቅ ለውጥ ቢሆንም፣ እንዲህ ዓይነቱ ተነሳሽነት በከተሞች አከባቢ ባሉ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የተወሰነ ነው። ነገር ግን 80% የሚሆነው ህዝብ የሚኖረው በገጠር አካባቢዎች ነው። የንፅህና መጠበቂያዎች አቅርቦት እጥረት እንዳይኖር ለገጠር ትምህርት ቤቶችም ትኩረት እንዲሰጥ እንጠይቃለን። በወር አበባ ወቅት ሊከሰቱ የሚችሉ ያልተጠበቁ ለውጦችን ለመቋቋም የሚያስችሉ ሌሎች አስፈላጊ የንጽሕና መጠበቂያ ዕቃዎች እንዲያሟሉና በቅርበት እንዲያገኙ እንጠይቃለን።

> “የንጽሕና መጠበቂያ ፓዶችን ማግኘት ቅንጦት ሳይሆን፤ እኔና እኩዮቼ ጤንነታችንን፣ ክብራችንንና በትምህርታችን ሙሉ ተሳትፎ የማድረግ አቅማችንን ለመጠበቅ የሚያስፈልገን ነው።"
>
> - የ11ኛ ክፍል ተማሪ፣ ከገጠር አካባቢ

በትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚገኙ መሠረተ ልማቶችን ማሻሻል ትምህርት ቤቶች በተሟላ መልኩ ተደራሽና ጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ አስፈላጊ ነው። ንፁህ ውሃ፣ የእጅ መታጠቢያ ቧንቧዎች፣ ለወንድና ለሴት እንዲሁም ለአካል ጉዳተኞች ተብለው የተለዩና ደህንነታቸው የተጠበቀ መጸዳጃ ቤቶች፤ እንዲሁም በሁሉም ትምህርት ቤቶች ውስጥ የኤሌክትሪክ ኃይል እንዲኖር እንጠይቃለን። እነዚህ ጉዳዮች ንፅህናችንን ለመጠበቅ እና ዘመናዊ የትምህርት ሂደት ለመተግበር አስፈላጊ ናቸው።

በተለይም በገጠር አካባቢዎች የሚገኙ የሕዝብ ትምህርት ቤቶችን ቁጥር በመጨመር እና በግጭት ወቅት የፈረሱ ትምህርት ቤቶችን መልሶ በመገንባት፤ በርካታ ሴት ልጆች ከሚኖሩበት አካባቢ ለትምህርት የሚጓዙትን ርቀት መቀነስ ያስፈልጋል። ይህም ለሴት ልጆች ደህንነትን ለማስጠበቅ እና የትምህርት ተደራሽነትን ለማሳደግ ይረዳል።

በትምህርት ቤቶች ውስጥ ቤተ መጻሕፍት፣ ቤተ ሙከራዎች፣ ለሴት ልጆች ደህንነታቸው የተጠበቁ የመመራመሪያ ስፍራዎች እንዲገነቡ ስንጠይቅ ልዩ ልዩ የትምህርት ፍላጎቶቻችንን ያሟሉልናል በሚል እምነት ነው።

## 3 በትምህርት ቤቶች ውስጥ እና በዙሪያቸው፤ እንዲሁም ከቤት እስከ ትምህርት ቤቶች ድረስ ያለው መንገድ ሰላምና ደህንነት ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ መሆን አለበት!

ትምህርት ቤቶች ደህንነታቸው የተጠበቀ እንዲሆንናምሴት ተማሪዎችን ከጥቃት ለመከላከል ተገቢው የጥበቃ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል። ጥብቅ የፀረ-ትንኮሳ ፖሊሲዎችን ማውጣት የሚደርሱብንን ጥቃቶች ያለፍርሀት ሪፖርት ማድረግ እንድንችል ያደርገናል። የማህበረሰብ መሪዎችንና የቤተሰብ አባላትን ያሳተፈ የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራሞች፣ ሴት ልጆችን ከጥቃት ለመከላከል፣ የትምህርት አካባቢን ሰላማዊና ደጋፊ እንዲሆን ለማድረግ ያግዛሉ።



> “የትግራይ ክልል እኩዮቼን በመወከል የምጠይቀው፤ ከምንም ነገር በላይ ሰላምና ደህንነት እንዲሰፍን ነው። እኔና ጓደኞቼ ማንም ሰው ጥቃት እንደማያደርስብን አምነን ሳንፈራ ወደ ትምህርት ቤት መሄድና ወደ ቤታችን መመለስ ይኖርብናል።"
>
> - የ12ኛ ክፍል ተማሪ ከከተማ አካባቢ

## 4 ሴት ልጆች ትምህርት እንዳይመዘገቡ እና በትምህርት ላይ እንዳይቆዩ የሚያደርጉ እንቅፋቶችን ማስወገድ

- የሴት ልጆች የትምህርት አስፈላጊነትን ለማስገንዘብ እንዲሁም አግላይና ጎጂ ባህላዊ እምነቶችን ለማስቀረት የተጠናከረ ሁሉን አቀፍ የህብረተሰብ ንቅናቄ ዘመቻዎች እንዲያከናወኑ ጥሪ እናቀርባለን።
- ሴቶች ልጆቻቸውን በማስተማር ስለሚያስገኟቸው ቤተሰባዊና ሀገራዊ ጥቅሞች በማስገንዘብ፤ ወላጆችና አሳዳጊዎች ለትምህርትና ጥናት ጊዜ እንዲኖረን የቤት ውስጥ ሥራዎችን እና ሌሎችን የመንከባከብ ኃላፊነቶችን ለማስቀረት የሚያስችል ግንዛቤ ማስጨበጥ አስፈላጊ ነው።
- በሁሉም የትምህርት ዘርፎች ላይ ተሳትፏችንን የሚያበረታቱ፣ ለትምህርታችን ስኬት የምናደርገውን ጥረት የሚያረጋግጡ፣ ለስርዓተ ጾታዊ ጉዳዩች ምላሽ ሰጪ የማስተማሪያ ዘዴዎች እንዲኖሩ እንሟገታለን።
- በትምህርት ጉዞዎቻችን ላይ ሊያነሳሱንና ሊመሩን ከሚችሉ ሴት አርአያዎች ጋር የሚያገናኙ የማስተማሪያ ፕሮግራሞች እንዲኖሩ እንዲሁም ፕሮግራሞቹ የሚመሩበት መዋቅሮች እንዲፈጠሩ እንጠይቃለን።
- የትምህርት ቤቶች የምገባ ፕሮግራም በአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች እንጂ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የለም። ይህ ድጋፍ ለሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች፤ በተለይም ለሴት ልጆች በጣም አስፈላጊ ነው ። ሴት ልጆች በትምህርት ቤት እንዲቆዩ፣ ደህንነታቸው እንዲጠበቅ እና በትምህርታቸው ላይ እንዲያተኩሩ ለመርዳት በሁሉም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የምገባ ፕሮግራም እንዲጀመር አጥብቀን እንጠይቃለን። በተጨማሪም ለሴት ልጆች የነፃ ትምህርት ዕድል የሚሰጡ ፕሮግራሞችን እና ቤተሰቦች ሴት ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት እንዲልኩ ለማበረታታት የገንዘብ ድጋፍ የሚሰጡ ፕሮግራሞች እንዲኖሩ እንጠይቃለን።

> “ ዩኒቨርስቲ የመግባት እድል እንዲኖረኝ እና የትምህርት ዕድል ላላገኙ እኩዮቼ አርአያ እንድሆናቸው እፈልጋለሁ። ትምህርት ለሁሉም ሰው እኩል ተደራሽ እንዲሆን ድምፄን አሰማለሁ።
>
> - የ 19 ዓመት ወጣት፤ ከገጠር አካባቢ[1]

## 5 መረጃ የማግኘትና የጤና አገልግሎት መብቶች፤ በዋናነት የስነ-ተዋልዶ ጤና (SRH) መብቶች ይከበሩ!

ምንም እንኳን ለእኛ አስፈላጊ ቢሆንም በማህበረሰባችን ውስጥ ስ ስነ-ተዋልዶ ጤና ማውራት እምብዛም የተለመደ አይደለም። በህገ መንግስቱ በቤተሰብ ህጉ፣ እንደተደነገገው የትምህርትና የጤና አገልግሎት እንዲሁም የስነ-ተዋልዶ ጤና መረጃ የማግኘት መብት እንዳለን ይገልጻል። በተጨማሪም የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ፣ ብሔራዊ የወጣቶች ፖሊሲ እና ብሔራዊ የአፍላና የወጣቶች የስነ-ተዋልዶ የጤና አገልግሎት ስትራቴጂ የስነ-ተዋልዶ ጤና አገልግሎትን እና የወጣቶችን የተለየ የጤና ፍላጎት በመገንዘብ በትምህርት ቤቶች ለእድሜያችን አግባብነት ያለው፣ የተሟላ የስነ-ተዋልዶ ጤና ትምህርት መሰጠት እንዳለበት ይደነግጋሉ። እንደዚህ አይነት መረጃዎች እኛን ሴት ልጆችን ስለሰውነታችን፣ መራቢያ አካላትና ስለስነ-ተዋልዶ ጤና መብቶቻችን በቂ እውቀት ለማግኘት፣ በእውቀት ላይ የተመሰረቱ ውሳኔዎችን እድንወስን እና ለራሳችን ጤንነት ቅድሚያ እንድንሰጥ ብቁ ያደርጉናል።

ስለሆነም፦

- በአገር አቀፍና በክልል ባለው የትምህርት ስርዓትና ፖሊሲ ውስጥ ባህልንና ወግን መሰረት ያደረገ አጠቃላይ የስነ-ተዋልዶ ጤና ትምህርት እና አገልግሎት እንዲካተት የትምህርት ሚኒስቴር እና የክልል ትምህርት ቢሮዎች ምላሽ እንዲሰጡ ጥሪ እናቀርባለን።
- የጤና አግልግሎት ተደራሽነታችንንን ለማረጋገጥ፣ የስነ-ተዋልዶ ጤና፣ የመራቢያ አካላት ጤንነት፣ የወሊድ መከላከያን፣ ጥንቃቄ በጎደለው ግንኙነት የሚተላለፉ የአባላዘር በሽታዎችን (STIs) ለማከላከል እና የአዕምሮ ጤናን ለማረጋገጥ የሚያግዙ የጤና አገልግሎቶችን ማግኘት ያስፈልገናል። ይህም የተሟላና ሚስጥራዊነቱን የጠበቀ፤ እንዲሁም የሴት ልጆችን የተለየ የጤና ፍላጎት የሚያሟላ እንዲሆን እንጠይቃለን።
- ለኛ ለሴት ልጆች ለጤናችንና ለስብእናችን የሚያስፈልገን ትክክለኛ የጤና መረጃና አገልግሎት ለማግኘት ምቹ ከባቢያዊ ሁኔታዎች እንዲፈጠርልን እንጠይቃለን።

## 6 ጾታን መሰረት ያደረጉ እና በሴት ልጆች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶች ይቁሙ!

ጾታን መሰረት ያደረጉ እና በሴት ልጆች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶች እኛን ሴት ልጆችን ያሳስበናል፤ ያስጨንቀናል። በተለይ እኛ ሴት ተማሪዎች ወሲባዊ ጥቃትን ጨምሮ ለእነዚህ ጾታን መሰረት ላደረጉ ጥቃቶች ተጋላጮች ነን። ወደ ትምህርት ቤት ስንሄድ እና ከትምህርት ቤት ስንመለስ ስጋታችን የበዛ ነው። ጾታዊ ትንኮሳዎች እና ዛቻዎች ደህንነታችንን አደጋ ላይ ከመጣላቸውም በላይ የትምህርት እድሎቻችንንም እያደናቀፉ ይገኛሉ። በበርካታ አካባቢዎች እየተከሰቱ ያሉት ግጭቶች ፍርሀታችንንና ጭንቀታችንን ይበልጥ አባብሰውታል። በመሆኑም፡

- ከጾታዊ ጥቃት እንድንጠበቅ፣ የጥቃቱ ፈጻሚዎች በወንጀላቸው ተጠያቂ እንዲሆኑ ለማድረግና ተጠቂዎች አስፈላጊውን የጤና፣ የህግ እና የስነልቦና ድጋፍ እንዲያገኙ ጠንካራ የህግ ማዕቀፎች እና የድጋፍ ስርዓቶች በአስቸኳይ ያስፈልጉናል።
- የጾታ ጥቃት በሴት ልጆች ላይ ስለሚያስከትለው መዘዝ የማህበረሰቡን ግንዛቤ ማሳደግ እንዲሁም አድልዎ የሚፈጥሩ ማህበራዊ ደንቦችን፣ ባህላዊ ልምዶችና ተግባራት፣ እንዲሁም የተዛቡ የስርዓተ-ጾታ አመለካከቶችን መለወጥ ያስፈልጋል።

> “ሊለወጡ በሚገቡ የተለመዱ የተለያዩ አይነት አመለካከቶች ተጎድተናል፤ ለምሳሌ ያህል፡ሴት ሲበዛ ጎመን ጠነዛ! ፤ ሴት ብታውቅ በወንድ ያልቅ! ፤ሴት ተምራ የት ትደርሳለች!እነዚህ የተለመዱ አመለካከቶችና አባባሎች እንዲሁም ተግባራት መለወጥ አለባቸው፤ የለውጡ ድምጽና አካል መሆን እፈልጋለሁ።”
>
> - 19 ዓመት ሴት ልጅ፤ ከከተማ አካባቢ[1]




- በሴት ልጆች ላይ ለሚፈፀሙ ጥቃቶችን ምንም አይነት ትዕግስትና ማለባበስ እንዳይኖር ለማድረግ የማህበረሰብ መሪዎች የመሪነት ሚና እንዲኖራቸው እነሱ የሚሳተፉባቸው ዘመቻዎችና ንቅናቄዎች እንዲካሄዱ ጥሪ እናቀርባለን።
- በተጨማሪም በተለይ በየቀኑ ወደ ትምህርት ቤት በምንሄድበትና በምንመለስበት ጊዜ ለጥቃት ተጋላጭነታችን ከፍ ያለ እንደሆነ እንገነዘባለን። ስለሆነም ይህን ለመከላከል ደህንነቱ የተጠበቀ የመጓጓዣ አማራጮች እንዲኖሩ የማህበረሰቡና የጸጥታ ሀይሎች ጥበቃ አስፈላጊነት የጎላ ነው።
- የመማር እድሎቻችንን የሚነጥቁ ጎጂ ባሕላዊ ልማዶች እንዲወገዱ አጥብቀን እንሟገታለን።
- የመማር መብቶቻችንን ከሚያሰናክሉ ህጻናትን የጉልበት ስራ ማሰራትና ብዝበዛ እንዲቀር ጥበቃ እንዲደረግልን እንጠይቃለን።
- የሕግ አስፈጻሚ አካላት (ፖሊስ፣ የፍትህ አካላት) ሴት ልጆችን ከጥቃት ለመከላከል ደህንነታቸው እንዲጠበቅ የወጡት ህጎችና ደንቦች እንዲያስከብሩ ደህንነቱ የተጠበቀ አካበቢ እንዲኖረን፤ ጥቃት ፈጻሚዎች ወደ ፍትህ እንዲቀርቡ የማድረግ ሀላፊነታቸውን እንዲወጡና ፍትህ እንዲረጋገጥ ተግተው እንዲሰሩ እንጠይቃለን።

## ለተግባራዊ የለውጥ እርምጃ የተደረገ ጥሪ

# ድምጻችን ይሰማ፤ ውክልናችን ይረጋገጥ!

ብዙ ጊዜ የእኛ የሴት ልጆች አይታዎቻችን፣ ውክልናችን አይከበርም፤ ድምጻችን አይደመጥም። በማህበረሰቡም ሆነ በትምህርት ቤት በጋራ የምንጠቀምበት ደህንነቱ የተጠበቀ ስፍራ ቢኖረን ያሉንን ልምዶች ሳንሸማቀቅ እንወያያለን፤ ልምዶቻችንን እንቀያየራለን። በሕይወታችን ላይ ለውጥ በሚያመጡ ጉዳዮች ላይ እንመክራለን። በዚህም መሰረት፦

·ለራሳችን እንድንናገርና በሌሎችም እንድንደመጥ እናሳስባለን። በመሆኑም ድምፃችንን የምናሰማበት እና የውክልናችንን ሚና የምናሳይበት ቦታ ማግኘታችን ወሳኝ ነው።

የአመራር ክህሎት ማሻሻል እና የብቃት ማጎልበት ፕሮግራሞች እኛን አካታች በሆነ መልኩ እንዲተገበሩ እንጠይቃለን። የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች፤ በህዝብ ፊት ንግግር የማድረግ ችሎታን እንዲሁም የውትወታና የተቋማዊ አመራር ክህሎቶችን ማዳበር ላይ የሚያተኩሩ እንዲሆኑ እንጠይቃለን።

እኛን በሚመለከቱ ሃገራዊ ፕሮግራሞች ውስጥ ከእቅድ ጀምሮ የመሳተፍ እድል እንዲኖረን እንሻለን። ይህም የወደፊት ህይወታችንን አቅጣጫ በመተለም ውስጥ የመሪነት ሚናን እንድንወስድ፣ ውክልናችንን እንድናጠናክር፣ በራስ መተማመናችንን እንድናሳድግና ንቁ ተሳታፊ እንድንሆን ያግዘናል።

በተጨማሪም አስተማሪዎች፣ አማካሪዎች፣ አርአያነት ያላቸው ግለሰቦች፣ የማህበረሰብ መሪዎች እና ወላጆች የእኛን ተነሳሽነት በመደገፍ፣ ሀሳባችን እንዲሰማና ከፍ ያለግምት እንዲኖረው የማድረግ ሀላፊነታቸውን እንዲወጡ እንጠይቃለን።



# 1 ጠንካራ ጥምረቶችን እና መድረኮችን መመስረት

አቅማችንን ለማጎልበት በጋራ መስራት  አስፈላጊ ነው። ከሌሎች ተመሳሳይ ሃሳብ ካላቸው አካላት ጋር ህብረትን በመፍጠር ሀብትን መጋራት እና አብሮ መስራት፤ ድጋፍ ያመጣል፣ የተለያዩ ልምዶችን ያሰባስባል፣ አንድነታችንን ያጠናክራል ብለን እናምናለን። ይህም የጋራ እንቅፋቶችን ማሸነፍ እና የሚያጋጥሙንን ልዩ ልዩ ተግዳሮቶች በጋራ ለመወጣት ያስችለናል። በትምህርት ቤቶቻችን እና በማህበረሰቡ ውስጥ ጠንካራ ጥምረት መመስረት ትብብርን ለማጎልበት እና አዎንታዊ ለውጥ ለመፍጠር መሰረት ይሆናል።

- በትምህርት ቤትም ሆነ በማህበረሰቡ ውስጥ በተለያዩ ክበቦችና ማህበራት መደራጀት እንፈልጋለን። ይህንን ለማድረግ አሁን ያሉትና ለወደፊት የሚደራጁ መዋቅሮች ሁሉ ለኛ ለሴት ልጆች ቦታ መስጠት አለባቸው ብለን እናምናለን። የተለያዩ መድረኮችና ኔትዎርኪንግ ዝግጅቶች በመካከላችን ትብብር እና የሃሳብ ልውውጥ እንዲኖር ምቹ ሁኔታን ይፈጥራሉ። አንድ ማህበረሰብ የመሆን ስሜትን ያጎለብታሉ።
- ሴት ልጆችን ታሳቢ ያደረጉ የዲጂታል መድረኮችን መፍጠር፤ ቴክኖሎጂን እና ማህበራዊ ሚዲያን በመጠቀም እርስ በርሳችን እንድንገናኝ፣ እንድንተባበርና የጋራ እንቅስቃሴዎችን ለማከናወን በሰፊው የጋራ ጥረቶች እንዲኖሩን ያግዘናል። በተጨማሪም ተሞክሮቻችንን፣ ገጠመኞቻችን እና በሚመለከቱን ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ተወያይተን ፍላጎቶቻችንና እይታችንን በማጉላት ተጽዕኖ እንድንፈጥር ያስችለናል። እንደዚህ አይነት መድረኮች እና ኔትወርኮች ለምናስበው የስርዓተ-ፆታ ለውጥ እና ተተኪ ትውልድ የመፍጠር ዕቅድ እድል ስለሚሰጡ እንዲጠናከሩ እንጠይቃለን።

## 2 የውትወታና እና የጋራ ውይይቶች መድረኮችን መፍጠር

- የውትወታና እና የጋራ ውይይቶችን በማዘጋጀት ጉዳዮቻችንን በፖሊሲ አውጪዎች እና ውሳኔ ሰጪዎች እንዲሰሙ ማድረግ በጣም አስፈላጊ ነው።
- ከሴት አመራሮች እና አርአያ ሊሆኑ ከሚችሉ ሌሎች ሴቶች ጋር፤ እንዲሁም በተለያዩ ትውልዶች መካከል የሚደረጉ ውይይቶች ለሴት ልጆች ጠቃሚ ምክረ ሀሳቦች እና ግንዛቤዎች የሚሰጡ በመሆናቸው ትኩረት ሊያገኙ ይገባል።
- ስኬቶቻችንን እና ድሎቻችንን ማክበር እንዲሁም ዋጋ መስጠት ለቀጣይ ስራዎች መነሳሳትን፣ ተሳትፎን ያበረታታል። ይህም የመነቃቃት ባህሪን ከማሳደጉም በላይ አቻ ለአቻ መደጋገፍን፣ ህብረትን ያጠናክራል።
- እኛ ሴት ልጆች ድምጻችን እንዲሰማ በምናደርገው ጥረት ሁሉ ወንድ እኩዮቻችን እና የማህበረሰቡ አባላት አጋር ሆነው እንዲሳተፉ መረዳዳትን እና ትብብርን በማጎልበት መብቶቻችንን የበለጠ የሚደግፍ አካባቢን ለመፍጠር እንወተውታለን።
- ለመብቶቻችን መከበር በምናደርገው ውትወታ ሰፊ የህብረተሰብ ክፍሎችን በብቃት ለመድረስ ታዳሚዎችን ለመሳብና ለማሳተፍ፤ የሚያስፈልጉንን የዲጂታልና የኦላይን ክህሎቶችን ለይቶ ማወቅ ተገቢ ነው።

## 3 የተገለሉ እና ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ ሴት ልጆችን ጥያቄዎች ማካተት



እኛ ሴት ልጆች አንድ ነን እንጂ አንድ አይነት አይደለንም! ስለሆነም ፍላጎቶቻችን እና ጥያቄዎቻችን የተለያዩ ናቸው፡፡ ጥያቄዎቻችንን እና ፍላጎቶቻችን እንደመጣንበት የማህበረሰብ ክፍል፤ የኢኮኖሚ ደረጃ፤ ሀይማኖት እና ባህል እንዲሁም አካላዊና ስነ-ልቦናዊ ሁኔታ ይለያያል፡፡

ፆታዊ ጥቃትንና ኢኮኖሚያዊ ብዝበዛን ጨምሮ ከደረሰብን ጠባሳ ለማገገም የሚረዱ በቂ ድጋፍ ሰጪ የአገልግሎት ስርዓቶች ባለመኖራቸው ለጥቃት የምንጋለጥበት ደረጃ የሁላችንም እኩል አለመሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ከኛ መሀል እንኳን ከመኖሪያ ቦታቸው ተፈናቅለው በጊዜያዊ መጠለያ የሚገኙ፣ የእለት ጉርስ የሌላቸው፣ ወደ ትምህርት ቤት የማይሄዱ በመኖራቸው የእነዚህ ሴት ልጆች ጥያቄዎች ለመድረስና ለመፍታት የተለየ አቀራረብና ዘዴ እንደሚያስፈልግ መረዳት ይቻላል፡፡

በመጠለያ ካምፖች ውስጥ የምንኖር እኛ ሴት ልጆች ለደህንነታችን እና የተረጋጋ ህይወት እንዳንኖር ቀላል የማይባሉ አደጋዎች ያጋጥሙናል፡፡ ስለሆነም ጥበቃ፣ የማህበራዊ አገልግሎት ጤና፣ የትምህርት መሳሪያዎች እና የስነ-ልቦና ድጋፍ ማግኘት ጊዜ የማይሰጥ ፍላጎታችን ነው፡፡

አካል ጉዳተኛ ሴት ልጆች ደግሞ ልዩ ፍላጎቶች ያለን በመሆኑ፣ በመጠለያ እጦት እና በማህበረሰቡ በሚደርስብን መገለል ምክንያት ትምህርታችን ላይ ተጨማሪ እንቅፋት ያጋጥመናል፡፡

የኢኮኖሚ ችግር ያለባቸው ሴቶች ደግሞ ያለገንዘብ እርዳታ ትምህርታቸውን ለመከታተል ይቸገራሉ፡፡ ስለሆነም፡-

- እንደደረሰብን ልዩ ጥቃት፣ ጉዳትና መገለል አይነት በተለይ ደግሞ በግጭት አካባቢ የምንኖር፤ በደረሱብን የተለያዩ አካላዊ እና የስነ-ልቦና ጥቃቶች በጽናት እንድናልፍ ችግሮቻችንን ያገናዘበ ድጋፍ እንዲደረግልን ጥሪ እናቀርባለን፡፡ የስነ-አእምሮ ጤና አገልግሎትና ከአእምሮ ጠባሳ ለማገገም የሚያስችሉ ፕሮግራሞችን ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ነው ፡፡

- በግጭት ምክንያት ትምህርታችንን ያቋረጥን ሴት ልጆች ወደ ትምህርታችን እንድንመለስ የሚያበረታቱ ስራዎች እንዲከናወኑና ጥቃት የፈጽሙ ሰዎች ለፍትህ እንዲቀርቡ፣ ተጠያቂ እንዲሆኑና እርምጃዎች እንዲወሰዱ ውትወታ እናደርጋለን፡፡

- ግጭቶች ባሉባቸውና በነበሩባቸው አካባቢዎች ያሉ ትምህርት ቤቶች ለሴት ልጆች አስተማማኝና ደህንነታቸው የተጠበቀ መሆኑ እንዲረጋገጥ፣ ትምህርት ቤቶች እድሳት ተደርጎላቸው እንዲከፈቱ ማድረግ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

> “እኔና ጓደኞቼ ከሁለት ዓመት በላይ ወደ ትምህርት ቤት አልሄድንም፡፡ ወደ ትምህርት ቤት ስንመለስ ሁሉም ነገር በጦርነት ፈራርሷል፡፡ ጦርነቱ ትምህርት ቤታችንን ብቻ ሳይሆን ምኞታችንን ጭምር አጨለመብን፡፡ ጥበቃና ደህንነት ማግኘት ያስፈልገናል፡፡"
>
> - የ19 ዓመት ልጅ፤ ከትግራይ ክልል[1]

# ለተግባራዊ የለውጥ እርምጃ የተደረገ ጥሪ

- መድሎና መገለል ለደረሰባቸው አካል ጉዳተኛ ሴት ልጆች፣ የትምህርት አገልግሎቶች ተደራሽ እንዲሆንላቸው የሚያስችሉ ፖሊሲዎች እንዲወጡ እና ተፈጻሚ እንዲሆኑ ድምጻችንን ያለማቋረጥ እናሰማለን።

> “አንዳንድ ጊዜ ለፈተና መቀመጥ ይከብደኛል፤ ምክንያቱም አካል ጉዳተኛ ለሆኑ ሴት ልጆች በቂና ምቹ መገልገያ የለም። ሁሉም የአካል ጉዳተኛ ሴት ልጆች አላማቸው ላይ ለመድረስ የበለጠ ትኩረት እንዲሰጣቸው እፈልጋለሁ።
>
> - የ20 ዓመት አካል ጉዳተኛ ልጅ

- እኛ የአርብቶ አደር ማህበረሰብ ሴት ልጆች ፍላጎቶቻችንን የሚያሟሉና ከአካባቢያችንን ጋር የሚስማሙ አማራጭ መሰረታዊ የትምህርት እድሎች እንዲስፋፉ ውትወታ እናደርጋለን።

> “የመጣሁት ከአርብቶ አደር ማህበረሰብ ሲሆን ከአካባቢያችንን ጋር የሚስማሙ አማራጭ መሰረታዊ ትምህርትን ማስፋፋት ለኑሮአችን በሚስማማ መንገድ የመማር እድል ይሰጠናል ብዬ አምናለሁ። የዕለት ተዕለት ኑሮአችንን የሚረዱ እና የተሻለ የወደፊት ሕይወት እንድንገነባ የሚያግዙ አማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ያስፈልገናል።”
>
> -የ18 ዓመት ከአርብቶ አደር አካባቢ)

- ጎጂ የሆኑ ባህላዊ ልማዶችን፤ በተለይም የህፃናት ጋብቻን እና የሴት ልጅ ግርዛት እንዲቆም እንጠይቃለን። በአርብቶ አደር ማህበረሰቦች ውስጥ ለምንኖር ሴት ልጆች ጥራት ያለው የትምህርት ተደራሽነት እንዲኖር እንጠይቃለን ።

> “ጎጂ ባህላዊ ድርጊቶች በተለይም በአርብቶ አደር አካባቢ የተስፋፋውን የልጆች ጋብቻ እና የሴት ልጅ ግርዛት እንዲቆም እና በአርብቶ አደር አካባቢ ያሉ ሴት ልጆች በሙሉ የትምህርት እድል እንዲኖራቸው እፈልጋለሁ።"
>
> -የ18 ዓመት ልጅ ከአርብቶ አደር አካባቢ

- በመጠለያ ካምፖች ውስጥ ለምንኖር ሴት ልጆች፤ በተለይም ወላጆቻችንን ወይም አሳዳጊዎቻችንን ላጣን፣ የጀመርነውን ትምህርት ለመቀጠል፣ እንዲሁም በጦርነት እና በተለያዩ ሰብአዊ ቀውሶች ምክንያት ትምህርት ቤት መግባት ለማንችል ሴት ልጆች ልዩ ትኩረት እንዲሰጠን እና ጥበቃ እንዲደረግለን እንጠይቃለን።

“ከምኖርበት አካባቢ ስለተፈናቀልኩ አሁን ስለምማርበት አዲስ የትምህርት ቤት ሁኔታ ለመረዳት ባለመቻሌ ብዙ ስቃይ ደርሶብኛል። የምናገኘው የትምህርት አይነት ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታችንን ከግምት ውስጥ የሚያስገባ መሆን አለበት።”

- የ 19 ዓመት ወጣት ሴት ልጅ ከተፈናቃይ ካምፕ

- ኢኮኖሚያዊ ችግር ላለብን ሴት ልጆች የኢኮኖሚያዊ ነፃነት ለማምጣት የሚረዱ የገንዘብ ድጋፍና ራሳችንን እንድንችል የሚያስችሉ የሙያ ሥልጠና ፕሮግራሞች እንዲኖሩ አጥብቀን እንጠይቃለን።

- መንግስት የትምህርት ተደራሽነት እና ደህንነት ላይ እንቅፋት የሚሆኑ ፖሊሲዎችን እንዲያሻሽልና ለሴት ልጆች የስርዓተ-ጾታ እኩልነት እና ጥበቃ ቅድሚያ እንዲሰጥ መስራት ይኖርበታል።፣

- የጤና ሚኒስቴር የጤና አገልግሎቶችን ከትምህርት አሰጣጥ ስርዓት ጋር በማዋሀድ አካላዊም ሆነ የአእምሮ ጤንነት ፍላጎቶቻችንን ማሟላትን ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። ልዩ ፍላጎቶቻችንን ለማሟላት ምሉዕ የሆነ የድጋፍ ፕሮግራሞችን ለመቅረጽ የሚያስችል በቂ ሀብትን የማሰባሰብ እና ውጤታማ ትግበራዎች እንዲከናውኑ እንጠይቃለን።



# ባለድርሻ አካላት ንቅናቄያችንን እንዲቀላቀሉ ጥሪ እናቀርባለን!

የአካባቢያዊ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች (CSOs)፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች (NGOs)፣ ዓለም አቀፍ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች (INGOs) እና የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶችን ጨምሮ ሁሉም ባለድርሻ አካላት በዚህ ወሳኝ ሴት ልጅን የማጎልበት እንቅስቃሴ ላይ እና የዚህን ማኒፌስቶ አፈፃፀም እንዲቀላቀሉ ጥሪ እናቀርባለን። እንዲህ ዓይነቱ የጋራ ጥረት እና ትብብር ውትወታችንን ያጠናክራል እንዲሁም የሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች የሴት ልጆችን ፍላጎቶች እና መብቶች ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲሟሉ ያደርጋል።

---

የፖሊሲ እና ውሳኔ ሰጪዎች፣ የየዘርፉ የመንግስት ሚኒስቴር መሰሪያ ቤቶች እንዲሁም ቢሮዎች ነባር ፖሊሲዎች እና ፕሮግራሞች እንዲተገብሩ፤ አዳዲስ ፍላጎቶቻችንን እንዲያሟሉ አስፈላጊውን ማሻሻያ እንዲያደርጉ ጫና እናደርጋለን።

---

ተሞክሮዎችን እና ቴክኒካዊ ድጋፍን እንዲሁም ጥረታችንን ለመደገፍ እና ትርጉም ያለው ለውጥ ለማምጣት ሀብቶችን መመደብ ተገቢ ነው።

---

የየአካባቢው መሪዎችን እና ቤተሰቦችን ለትምህርት ቅድሚያ እንዲሰጡ እና ጎጂ ልምዶችን እንዲቃወሙ ማበረታታትና ማስቻል ሴት ልጆችን የሚያከብር እና ጥበቃ የሚያደርግ ባህላዊ ለውጥ ለማምጣት አስፈላጊ ነው።

---

ሴት ልጆች ላይ ያተኮሩ ፖሊሲዎችና እቅዶች መተግበር በትምህርት፣ በጤናና በማህበራዊ ህይወት መጎልበትና መስፋፋት ረገድ ከፍተኛ መሻሻል ሊያመጣ ይችላል። ይሁን እንጂ እነዚህ ተነሳሽነቶች ውጤታማ መሆናቸውንና የሴት ልጆችን ፍላጎቶች የሚያሟሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ፤ ተፅዕኖዎቻቸውን ለመቆጣጠርና ለመገምገም ጠንካራ ዘዴዎች ያስፈልጉናል።

---

በህብረተሰባችን ውስጥ ግልፅነትን እና መተማመንን ለማጎልበት በሁሉም ባለድርሻ አካላት መካከል ተጠያቂነት በጣም አስፈላጊ ነው ።

---

እነዚህን የጋራ እርምጃዎች በመውሰድ፣ ለኢትዮጵያውያን ሴት ልጆች ሁሉ ብሩህ የወደፊት ሕይወት ለመገንባት የእናንተን ድጋፍ እና እርዳታ እንጠይቃለን።




# በአንድነት ተነስተናል፤ ድምፃችን ይሰማ!

[1] በዚህ ሰነድ ውስጥ 19/20 የሆነን ሴት ልጆች የእድሜያችን ከፍ ማለት በተለያዩ ሁኔታዎች ምክንያት (ጦርነት፣ ግጭትና ቀውሶች) ትምህርት በማቋረጣችን ነው

# የኢትዮጵያ ሴት ልጆች ማኒፌስቶ
2017

MALALA FUND SUPPORTER

EDUCATION CHAMPION NETWORK ETHIOPIA

NEWA

+251952048277 newaethiopia@gmail.com
In front of Gibson Academy,Kebele 24,
Addis Abeba, Ethiopia
P.O Box 19357

**www.newaethiopia.org**

design & print: creativeprofusion.com